በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ቁጥር OFAGF-03.24/12/7
ቀን 02/08/2015

ለክብርት ወ/ሮ አለምፀሐይ ጳውሎስ

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ኃላፊና

የካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስትር

ለክቡር ኢንጅነር ወርቁ ጋቸና

የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- የቀድሞው ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት የ2014 (ሀምሌ1 እስከ ህዳር 30/2014) በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል

በርዕሱ የተጠቀሰውን የቀድሞው ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት የ2014 (ሀምሌ1 እስከ ህዳር 30/2014) በጀት ዓመት የኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 10 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 23 ገጽ የሂሣብ ሪፖርቶች በድምሩ 33 ገጽ የያዘ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

መሠረት ታደሰ
የፌዴራል ም/ዋና ኦዲተር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የቀድሞው ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት
የ2014(ሀምሌ1 እስከ ህዳር 30/2014) በጀት ዓመት ሂሳብ
የኦዲት ሪፖርት

መጋቢት/2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የቀድሞው ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት

የ2014(ሀምሌ1 እስከ ህዳር 30/2014) በጀት ዓመት ሂሳብ

ኦዲት ሪፖርት

የቀድሞው ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል።

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የቀድሞው ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል። ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል።

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል።

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የቀድሞው ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የቀድሞው ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት የሂሳብ ሪፖርቶች፡-

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች(Basic of Audit Opinion)፣

የቀድሞው ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

1. ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ የደመወዝ ክፍያ፣

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 10 ከቁጥር 1-10 በተዘረዘረው መሰረት የመንግስት ሰራተኞች ደመወዝ ክፍያ መፈጸም እንዳለበት ያዛል፡፡ በዚህም መሰረት የቀድሞው ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩቱ ሰራተኞች ደመወዝና ጥቅማጥቅም ክፍያ መመሪያውን ተከትሎ መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በበጀት ዓመቱ የነበሩ የኢንስቲትዩቱ የሰራተኞች ብዛት የሚያሳይ ማስረጃ፣
- በበጀት ዓመቱ በጡረታ፣ በሞትና በሌሎች ልዩ ልዩ ምክንያቶች ከስራ የተለዩ ሰራተኞች ዝርዝር ማስረጃ፣
- በበጀት ዓመቱ በሹመት ወይም በዝውውር የተመደቡ ካሉ ማስረጃ፣
- ሰራተኞች ስራ ላይ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣
- የመ/ቤቱ የደመወዝና ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞች የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንን የሰራተኞች አዋጅ ተከትለው የወጡ የውስጥ መመሪያዎች፣

ለኦዲት እንዲቀርቡ በተደጋጋሚ ቢጠየቅም ሊቀርብ ባለመቻሉ በድምር ብር 22,314,855.92 ከሃምሌ 1/2013 እስከ ህዳር 30/2014 ዓ.ም ያለው የኢንስቲትዩቱ የደመወዝና ጥቅማጥቅም ክፍያዎች ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

2. የውሎ አበል ቅጽ በትክክል ሳይሞላ የተፈጸመ እና ያለአግባብ የተከፈለ የውሎ አበል፣

የመንግስት ሠራተኞች የአገር ውስጥ የቀን ውሎ አበል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 3/2012 አንቀጽ 9 ተራ ቁጥር 1 እና 4 ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ከመደበኛ የሥራ ቦታ ውጭ ሌላ ሥራ ቦታ ለስራ ጉዳይ ከመላኩ በፊት የቀን ውሎ አበል መጠየቂያ፣ መክፈያና መፍቀጃ ቅጾች ለጉዳዩ አግባብ ባለው ሠራተኛ ወይም የሥራ ኃላፊ እንዲሞሉ ይደረጋል፣ እንዲሁም በተራ ቁጥር 4 የቀን ውሎ አበል ክፍያ እንዲጸድቅለት የሚጠይቅ የስራ ክፍል ኃላፊ የማስክ ጉዞው ሪፖርት መቀበሉን

የሚያረጋግጥ መግለጫ በማጽደቂያ ሰነዶች ላይ ማመላከት እንዳለበት መመሪያው ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም በአንቀፅ 6 ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ከመደበኛ የስራ ቦታው ውጪ ወደ ሆነ ሌላ የሥራ ቦታ ለሥራ ጉዳይ ሄዶ መሥሪያ ቤቱ የምግብ ወይም የመኝታ አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ የተሰጠው የአገልግሎት ሂሳብ ከሚከፈለው የቀን ውሎ አበል ላይ ተቀናሽ እንደሚሆን ይገልጻል፡፡

ይሁን እንጅ የቀድሞው የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት የውሎ አበል ክፍያውን በመመሪያው መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በድምር ብር 181,800.00 የውሎ አበል ክፍያ ሲፈጸም ሰራተኞች የውሎ አበል ክፍያ ቅፅ ላይ የደመወዝ መጠን የማይሞላ፣ በጉዞ ላይ የቆዩባቸው ቦታዎች (ለቁርስ፣ ለምሳ፣ ለዕራት) መግለጫ ሰንጠረዥ ላይ የተጠቀሙበት ቦታ መቀመጥ ሲገባው ጠቅላላ ድምር ብቻ በመቀመጡ የክፍያውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣
- በተጨማሪም ለሰራተኞች የውሎ አበል ለቁርስ፣ ለምሳ፣ ለእራት እና ለአልጋ ሙሉ አበል የተከፈለ ቢሆንም በድጋሚ የአልጋ አበል በድምር ብር 171,099.90 ያለ አግባብ በደረሰኝ በማወራረድ መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ የዳረገ መሆኑ፣

በአጠቃላይ ድምር ብር 352,899.90 መመሪያውን ሳይከተል ያለአግባብ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

3. <u>ባልተሟላ ማስረጃ ክፍያ የተፈፀመ በመሆኑ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ የወጪ ሂሳብ፣</u>

የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 9 ማንኛውም ክፍያዎች ሲፈፀሙ ለወጪ ሒሳቦች ተገቢው የወጪ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ብሎ ከዘረዘራቸው ውስጥ በተ/ቁጥር 1 ላይ ለተገዛ ዕቃ ዕቃው እንዲገዛ ወይም አገልግሎት እንዲሰጥ ትዕዛዝ የተሰጠበት ማስረጃ መኖሩን፣ ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መሟላት እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ የቀድሞው ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት፡-

- በቀን 26/01/2014 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 6742 በሂሳብ መደብ 2221103 ብር 74,999.32 የሆቴል መስተንግዶ የአገልግሎት ግዥ በማከናወን ክፍያ ሲፈጸም ለምን ያህል ሰዎች መስተንግዶ እንደቀረበ፣ አገልግሎቱን ያገኙት እነማን እንደሆኑና ለስንት ቀን አገልግሎቱ

እንደተሰጠ የሚገልጽ የግዥ ትዕዛዝ መጠየቂያ ሳይኖር ለኢካስ ትሬዲንግ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣

- በቀን 04/01/14 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 6629 በሂሳብ መደብ 2221102 ብር 76,997.00 የአየር ትኬት ግዥ ከላሊበላ የጉዞ ወኪልና አስጎብኝ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና በቀን 18/12/14 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 6534 በሂሳብ መደብ 2221102 ብር 39,637.00 የአየር ትኬት ግዥ ከባቲ የጉዞ ወኪልና አስጎብኝ ኤም ጂ ታየር ኃ/የተ/የግ/ማህበር በማከናወን በድምር 116,634.00 ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም የተጓዦች ማንነትና የሄዱበት ቦታ/ሀገር የሚገልጽ ማስረጃ ሳይኖር ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣

በአጠቃላይ ድምር ብር 191,633.32 ለተፈጸመ ወጪ ትክክለኛና የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ክፍያ የተፈጸመ በመሆኑ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

4. <u>ለኦዲት ያልቀረቡ የወጪ ሂሳቦች፣ የጨረታ ሰነዶች እና የውል ስምምነቶች፣</u>

የመቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል አምስት ንዑስ አንቀጽ 17 የተመርማሪዎች ግዴታ በሚለው ርዕስ ስር የፌደራል ዋና ኦዲተር የመሥሪያ ቤቱ ኦዲተሮች ወይም የፌደራል ዋናው ኦዲተር ወኪሎች ለምርመራ ጠቃሚና አስፈላጊ የሚመስሏቸውን መጻሕፍት፣ መዛክሮች፣ መዝገቦች፣ ሰነዶችና ሌሎች የጽሑፍና የቃል መረጃዎች ሁሉ ሲጠይቁ የተጠየቀው ግለሰብ፣ ሠራተኛ ወይም ባለሥልጣን በትክክልና በተሟላ አኳኋን ወዲያውኑ የማቅረብ ግዴታ አለበት ይላል፡፡ በተጨማሪም በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ 2002 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 ቁጥር 23 መሰረት የግዥ ክፍል የግዢ ሰነዶችን ይይዛል፣ ይጠብቃል፣ ከሚመለከታቸው ህጋዊ አካላት ማብራሪያ ሲጠየቅ ተገቢውን ማብራሪያ ይሰጣል ይገልጻል ያላል፡፡

ይሁን እንጂ የቀድሞው ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት፡-

- በድምር ብር 542,632.10 የያዙ የወጪ ሂሳብ የሰነድ ማስረጃዎች እና
- በድምር ብር 4,117,002.81 የያዘ የጨረታ ሰነድና የውል ስምምነት የሰነድ ማስረጃዎች፣

ለኦዲት እንዲቀርብ በኦዲት ወቅት በተደጋጋሚ ቢጠየቅም ባለመቅረቡ የወጪ ሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

5. <u>የመነሻ የሂሳብ ምዝገባ፣ ባልተለመደ የሂሳብ ምዝገባ የተመዘገቡ ሂሳቦች በተመለከተ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም በክፍል ሁለት 6 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 (ለ) የእያንዳንዱ የሂሳብ መደብ እንቅስቃሴ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን (ዴቢት ወይም ክሬዲት) መያዝ እንዳለበት መመሪያው ያስቀምጣል፡፡ በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 9 የሂሳብ መዝጊያ በሚለው ስር ፊደል (መ) የቋሚ ሂሳብ ሚዛን የሳጥን ሂሳብ በባንክ ያለ የውጭ ምንዛሬ፣ በሌተር ኦፍ ክሬዲት የተገደበ ሂሳብ፣ የተከፋይ፣ ተሰብሳቢ እና የተጣራ ሃብት ሂሳቦች ወደ ቀጣዩ በጀት አመት መተላለፍ አለባቸው ይላል፡፡ የቀድሞው ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በ2013 ዓ.ም መጨረሻ ተመዝግበው የሚታዩ/የነበሩ/ የቋሚ ሂሳቦች ወደ 2014 ዓ.ም በጀት ዓመት በትክክል መተላለፋቸውንና የሂሳብ ሚዛናቸውን/Normal balance side/ ጠብቀው መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. <u>የመነሻ የሂሳብ ምዝገባን በተመለከተ፡-</u>

- የሂሳብ መደብ 6172105 (withholding tax payable) በ2013 ዓ.ም በጀት ዓመት መጨረሻ የሂሳብ ሪፖርት ላይ ብር 212,971.34 የሚታይ ቢሆንም ወደ 2014 ዓ.ም በጀት ዓመት ያልዞረ መሆኑ፣
- በሂሳብ መደብ 6174208 (vat payable) ብር 781,965.17 በ2013 ዓ.ም በጀት አመት መጨረሻ የሂሳብ ሪፖርት ላይ የሚታይ ቢሆንም ወደ 2014 ዓ.ም በጀት ዓመት ያልዞረ መሆኑ፣
- በሂሳብ መደብ 6175101 (Retention) ብር 429,438.80 በ2013 ዓ.ም በጀት አመት መጨረሻ የሂሳብ ሪፖርት ላይ የሚታይ ቢሆንም ወደ 2014 ዓ.ም በጀት ዓመት ያልዞረ መሆኑ፣
- የሂሳብ መደብ 5217205 (pre payement to suppliers) ብር 2,250.18 በ2013 ዓ.ም በጀት ዓመት መጨረሻ የሂሳብ ሪፖርት ላይ የሚታይ ቢሆንም ወደ 2014 ዓ.ም በጀት ዓመት ያልዞረ መሆኑ፣

2. <u>ባልተለመደ የሂሳብ ምዝገባ የሚታይ ሂሳቦች ማስተካከያ በተመለከተ</u>

- በሂሳብ መደብ 5212101(cash at bank budgetary account) ብር 5,080,952.70 በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ የሂሳብ ሚዛኑን ሳይጠብቅ በክሬዲት ተመዝግቦ የሚገኝ ሲሆን በ2014 ዓ.ም በጀት ዓመት

ሲመዘገብ በዴቢት ባላንስ ተመዝግቦ የተገኘ ቢሆንም የተስተካከለበትን ምዝገባ የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣

- የሂሳብ መደብ 6172202 (sundry creditor) በድምር ብር 2,087,179.03 በ2013 ዓ.ም በጀት ዓመት መጨረሻ የሂሳብ ሪፖርት ላይ በክሬዲት ተመዝግቦ የሚታይ ቢሆንም መጋቢት 30 2014 ዓ.ም በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርት ላይ የሂሳብ ሚዛኑን ሳይጠብቅ በዴቢት ባላንስ የሚታይ ቢሆንም የተስተካከለበትን ምዝገባ የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- በሂሳብ መደብ 5212601(deposit in transit) ብር 4,393,365.69 በ2013 ዓ.ም በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ የሂሳብ ሚዛኑን ሳይጠብቅ በዴቢት ተመዝግቦ የሚገኝ ሲሆን በ2014 ዓ.ም በጀት ዓመት ሲመዘገብ በክሬዲት ባላንስ ተመዝግቦ የተገኘ ቢሆንም የተስተካከለበትን ምዝገባ የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- የሂሳብ መደብ 7111101 (Net asset/equity) ብር 1,076,889.78 በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ባልተለመደ የሂሳብ እንቅስቃሴ ተመዝግቦ የሚገኝና ወደ 2014 በጀት ዓመት ያልዞረ ሂሳብ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 5 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ የሆኑ ምክንያቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል ያሳያሉ በማለት አስተያየት መስጠት አልተቻለም፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል።

<u>ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች(Emphasis matter)፣</u>

1. <u>ያለሂሳብ መደቡ የተመዘገበና በአንድ ሰው ተዘጋጅቶና ጸድቆ ክፍያ የተፈጸመ የወጪ ሂሳብ በተመለከተ፣</u>

   የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም በክፍል ሁለት አንቀፅ 6 ተራ ቁጥር 4 ላይ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸው በጀትና የወጣውን ወጪ በሚያሳይ መልኩ ተለይቶ በተሰጠ የበጀት መለያ መደብ ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው ይገልጻል:: በተጨማሪም የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 14 ተራ ቁጥር 4 መሠረት ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረብና ስልጣን ባለው አካል መፈቀድ እንዳለበት መመሪያው ይገልጻል፡፡ በመሆኑም የቀድሞው ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት በመመሪያው መሰረት እየመዘገበ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

   በድምር ብር 1,652,356.31 ከሂሳብ መደቡ ውጪ በሌላ የሂሳብ መደብ ተመዝግቦ የተገኘ ከመሆኑ በተጨማሪ ሂሳቡን ያዘጋጀው ባለሙያና ያፀደቀው ኃላፊ በአንድ ሰው የተፈረመ መሆኑን በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል።

2. <u>ስራ ላይ ያልዋለ በጀትን በተመለከተ፣</u>

   የፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀጽ 12(1) ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት መሥሪያ ቤቱ በጀቱን የሚቆጣጠር መሆኑን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተፈቀደው ብር 290,370,742.00 (ከሃምሌ 1, 2013 እስከ ህዳር 30, 2014) ባሉት ወራቶች ከ10% በላይ ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር፣

ከመደበኛ በጀት ብር 89,732,545.08፣ ከካፒታል በጀት ብር 153,669,464.49 በድምር ብር 243,402,009.57 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

3. <u>የሰነድና ንብረት ርክክብን በተመለከተ፣</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የገንዘብ ሚኒስቴር በቀን 27/1/2014 በቁጥር በመ36/6/1 በአደረጃጀት የታጠፉ፣ የተዋሃዱ፣ የተለያዩና አዲስ ለተፈጠሩ መ/ቤቶች ለእያንዳንዳቸው የፌዴራል መ/ቤት የሚጠበቅ ተግባርና ኃላፊነት በዝርዝር የሚገልጽ መመሪያ አውጥቷል፡፡ በዚህም መሰረት የተዋሃዱ መ/ቤቶች ለ2014 በጀት አመት ከጸደቀው በጀት ዉስጥ እስከ መስከረም 30/2014 ድረስ ያለዉን የፋይናንስ አጠቃቀም በተናጠል ዘግቶ የሂሳብ ሪፖርት እና የዉስጥ ኦዲት በማስመርመር ሪፖርቱን ለገንዘብ ሚኒስቴር ማሳወቅ፣ የሂሳብ ሰነዶቹን ኦዲት ከተደረጉ በኋላ ለተዋሃደው መ/ቤት ማስረከብ፣ በአዲስ ስያሜው መሰረት የባንክ አካዉንት መክፈትና ሂሳቡን እንዲያንቀሳቅስ የባንክ ዉክልና መስጠት፣ የተዋሃዱ መ/ቤቶች በተናጠል ሲጠቀሙበት የነበረዉን የባንክ አካዉንት መዝጋትና በተዋሃደው አዲስ መ/ቤት ስም ዉህደቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ የክፍያ እና የበጀት ጥያቄ ማስተናገድ እንዲቻል ደብዳቤ ማቅረብ እንዳለባቸው ያዛል፡፡ በተጨማሪም የተዋሃዱ መ/ቤቶች በተናጠል የንብረት ቆጠራ ኮሚቴ በማቋቋም ቆጠራ ማካሄድ፣ መመሪያ ቁጥር10/2003 በሚያዘው መሰረት ርክክብ መፈጸምና በዉህደቱ መሰረት ሊተርፉ የሚችሉትን ተሽከርካሪዎች፣ ቋሚ እቃ እና የማይጠቀሙበትን ቢሮ ለገንዘብ ሚ/ር ማሰወቃቸዉን በማረጋገጥ በየመ/ቤቱ ያሉ የዉስጥ ኦዲት የስራ ክፍሎች ለገ/ሚኒስቴር ማሳወቅ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ በዚህም መሰረት የቀድሞው የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ለአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት መመሪያዉን ተከትሎ ርክክብ ማድረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በ2014 ለቴክኖሎጅና ኢኖቬሺን ኢንስቲትዩት የተፈቀደው በጀት እስከ የካቲት 22 ዝውውር ያልተደረገና የካቲት 22 ዝውውር ሲደረግም ሙሉ ለሙሉ ወደ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት በጀቱ ያልተላለፈ መሆኑ፣

- እስከ መስከረም 30 ድረስ ያለው የፋይናንስ አጠቃቀምና የሂሳብ ሰነዶች ኦዲት ተደርገው ርክክብ መደረግ ሲገባቸው ዘግይተው ርክክብ የተደረጉና ሙሉ ለሙሉ ርክክብ ያልተደረጉ መሆናቸው፣
- የቀድሞው የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት ሲጠቀምበት የነበረዉን የባንክ አካዉንት ከመስከረም 30 በኋላ መዝጋትና ዉህደቱ እስከ ሚጠናቀቅ ድረስ ለአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት የክፍያና የበጀት ጥያቄ ማስተናገድ እንዲችል የዉክልና ደብዳቤ መስጠት ሲገባው ያልተሰጠ መሆኑና እስከ ህዳር 30 ክፍያ ሲፈጸም ከመቆየቱ በተጨማሪም እስከ መጋቢት 30 ቋሚ የሂሳብ አካዉንቶች ሲንቀሳቀሱ የቆዩ መሆኑ፣
- ከቀድሞው የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት ሙሉ ንብረት ወደ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ሲተላለፍ ርክክቡ በመመሪያው መሰረት መከናወኑን በዉስጥ ኦዲት ሳይረጋገጥ ርክክብ የተደረገ መሆኑ፣

በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)፣

1. የክትትል ኦዲት በተመለከተ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በየበጀት ዓመቱ የኢንስቲትዩቱን ሂሳብ ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የኢንስቲትዩቱን ተገቢውን እርምጃ የወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፦

የ2013 በጀት ዓመት ለኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ከተሰጣቸው ገንዘብ ውስጥ በልዩነት የታየውን የገንዘብ መጠን በዶላር $125.43 ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ያልተመለሰ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት